17ኛ ዓመት ቁጥር 180 2017 ዓ.ም በነፃ የሚታደል

# ገቢ ስልሣት


## በውስጥ ገጾቻችን

“የገቢው ዘርፍ ትልቁ የሀገሪቱ የትራንስፎርሜሽን አካል በመሆኑ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት ይኖርብናል”



ገጽ 3

“በስልክ ጠርተን አንሸልምም!”

ገጽ 4

ባለ ልዩ መለያ ደረሰኝ

ገጽ 4

ሕግ ወደ ኋላ ይሠራ ይሆን?

ገጽ 8







## የተቃና የትሪሊዮን ጉዞ

በሽመልስ ሲሳይ

በየትኛውም ሀገር ታክስ እና ቀረጥ መሰብሰብ የመንግሥት ተግባር ነው፡፡ በዚሁም ሁሉም ሀገራት ይህንን ተግባር እና ኃላፊነት እየተወጡ ይገኛል፡፡ በሀገራችን ይህንን ኃላፊነት እንዲወጡ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተቋማቱም ይህንን ተግባር እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣታቸው በየዓመቱ የገቢ አፈጻጸም እያደገ መጥቷል፡፡

ባሳለፈነው የ2016 በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ ታክስ እና ቀረጥ 512.83 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 96.88 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ በ2017 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ደግሞ ከሀገር ውስጥ ገቢ እና ከውጪ ንግድ ቀረጥ 451 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 101.9 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

ይህም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ106.7 ቢሊየን ወይም 110 በመቶ ብልጫ እንዳለው የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት ዓይናለም ንጉሴ የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት አፈጻጸም ግምገማ ወቅት ገልፀዋል፡፡

በተናጥል ስንመለከተው ከሀገር ውስጥ ታክስ 247.7 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 97.2 በመቶ ማሳካት ሲቻል በአንጻሩ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ 203.8 ቢሊዮን ብር



ክብርት ዓይናለም ንጉሴ

ወደ ገፅ 2 ዞሯል



ክቡር ደበሌ ቀበታ

## መንግሥት ሊያጣ የነበረ ከ107 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን ተቻለ

በሰሎሞን ወርቁ

የጉምሩክ ኮሚሽን ወደ ሀገር የሚገቡ እና ከሀገር የሚወጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ በተሰጠው ኃላፊነት እና ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ቀረጥ እና ታክስን በመሰብሰብ አገልግሎት እየሰጠ ገቢን ለሀገር እያስገባ ከመሆኑ በተጨማሪ ኅብረተሰቡን ኮንትሮባንድ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እየከናወነ ይገኛል፡፡

ኮሚሽኑ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ባቀረበበት ወቅት “በተለይም ኮንትሮባንድና ንግድ

ወደ ገፅ 2 ዞሯል

## የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚደግፍ ገቢ መሰብሰብ አለበት

በሰሎሞን ደግአረገ

የገቢ ልዕልናን ማስቀጠል ብሔራዊ ክብር እና ሀገራዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ ስለሆነ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊደግፍ የሚችል ዘላቂነት ያለው ገቢ መሰብሰብ እንዳለበት የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት ዓይናለም ንጉሴ በጅማ ከተማ በተካሄደው የፌደራልና የክልል የፋይናንስ፣ የገቢዎች እና የፕላን መሥሪያ ቤቶች የምክክር መድረክ ገለጹ፡፡

ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ ያለ የገቢ አሰባሰብ እና የመፈጸም አቅም እንደሚስተዋል የገለጹት ሚኒስትሯ ነገር ግን ከምንፈልገው አኳያ በጣም ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል





ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተቋም በልህቀት፤ ገቢ በስኬት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ በመቅረጽ ሁሉን አቀፍና አካታች የምጣኔ ሀብት እድገት ለማምጣት ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: ያም ሆኖ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ መተግበሩ ሀገራችን ከሌሎች ሀገራት በተሻለ ሁኔታ ዕድገት ለማስመዝገብ አስችሏታል:: በቀጣይ ዓመታትም ይህ ዕድገት እንደሚቀጥል የዓለም ባንክ እና ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት ትንበያዎቻቸውን አስቀምጠዋል::




ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ታሳቢዎች መካከል የሀገር ውስጥ ገቢ ማሻሻያ ይገኝበታል:: ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የመንግሥት የገቢ አሰባሰብ ከዓመት ወደ ዓመት መሻሻሎች ተስተውሎበታል:: ለአብነት በ2017 መጀመሪያ በግማሽ ዓመት ከሀገር ውስጥ ገቢ እና ከውጪ ንግድ ቀረጥ 151 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 101.9 በመቶ ማሳካት ተችሏል:: ከታክስ የሚሰበሰብ ገቢ ከአጠቃላይ የመንግሥት ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል:: ይህ የሀገር ውስጥ ገቢ የሀገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት በዘላቂነት በማስቀጠል የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና የልማት ሥራዎችን ፋይናንስ ለማድረግ ዋነኛውና አስተማማኝ የሆነው የገቢ ምንጭ መሆኑ ይታወቃል::

ከላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው የፌዴራል መንግሥት የገቢ አፈጻጸም በየዓመቱ እደገት እያሳየ መጥቷል:: ይሁን እንጂ አፈጻጸሙ በሁለት ዋና ዋና መለኪያዎች ማለትም ከመንግሥት ወጪ አሸፋፈን አኳያ እና የታክስ ገቢ ለአጠቃላይ የሀገራዊ ምርት ጥምርታ ያለውን አፈፃፀም ማሻሻል ይጠይቃል።

ስለሆነም ኢኮኖሚ የሚያመነጨዉን ገቢ አሟጦ በመሰብሰብ የመንግሥትን የወጪ ፍላጎት ለመደገፍ እና የታክስ ገቢ ከሀገር ውስጥ ምርት ጥምርታ አንጻር ያለውን ድርሻ ለማሻሻል እና መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የተጀመረው የገቢው ዘርፍ የሪፎርም ሥራ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

ከዚህ አንጻር መንግሥት የተለየዩ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ የሀገር ውስጥ ገቢ አሰባበሰብን በሚፈለገው ደረጃ በማሳደግ እና የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ጥመርታ ንፅፅር የሚያሽቆለቁልበትን ምጣኔ ለመቀነስ ብሎም ዕድገት ማስመዝገብ እንዲጀምር በርካታ የታክስ ማሻሻያ ሥራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል።

ከ2017-2021 የመንግሥት የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማዕቀፉ የታክስ ገቢ እንደ አንድ የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢ ተወስዷል። የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለታክስ ገቢ አቅም በየታክስ ዓይነቱ የሚኖራቸው እንደምታ በዝርዝር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ በትንበያ ሞዴሉ እንደዋነኛ ታሳቢ ተደርጓል።

ከላይ እንደ መንደርደሪያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ዳራ ለማመላከት የተሞከረው የገቢዎች ሚኒስቴር የሀገር ውስጥ ገቢ ከጠቅላላ ሀገር ውስጥ ምርት አንጻር ያለውን ጥምርታ ለማሻሻል በታክስ አስተዳደር መከናወን የሚገባቸው ሥራዎች በመለየት ሁሉን አቀፍ ማሻሻያዎች እና ሪፎርሞች ማድረግ የሚያስችል ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የታክስ ስትራቴጂ ወደ ትግበራ ምዕራፍ ገብቷል።

በትግበራ ምዕራፉ የገቢ አሰባሰቡን ሊጎዱ የሚችሉ ከደረሰኝ እና ከሕገ-ወጥ ንግድ ጋር የተያያዙትን ችግሮች በቅንጅት መቅረፍ ይጠበቃል። በተጨማሪ፣ ህቡዕ ኢኮኖሚ ውስጥ ተዋናይ የሆኑ ሕገ-ወጦችን በመከታተል ወደ ታክስ ሥርዓቱ መጥተው ተገቢውን ታክስ እንዲከፍሉ ማስቻል ይገባል። ከዚህ ባሻገር፣ የገቢ አሰባሰቡን ሊሸረሽሩ የሚችሉና የዘርፉን መልካም ስም የሚያጠለሹ ሌብነትን እና ብልሹ አሰራሮችን በጋራ ጥረት ለማስተካከል መሥራት ይጠበቃል።

## መንግሥት ሊያጣ የነበረ ከ107...

ከገፅ 1 የዞረ

ማጭበርበርን በመከላከል እና በመቆጣጠር ዙሪያ በሁሉም ዘርፎች ተጨባጭ ውጤቶችና ስኬቶች ተመዝግበዋል።" ብሏል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በግምገማው ወቅት እንደገለጹት፣ ባለፉት ስድስት ወራት 7.38 ቢሊዮን ብር የሚገመቱ የገቢ ኮንትሮባንድ እና 1.57 ቢሊዮን ብር የወጭ ኮንትሮባንድ በድምሩ 8.95 ቢሊዮን ብር ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የኮንትሮባንድ እቃዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስረድተዋል።

በኮንትሮባንድ ዝውውር የተጠረጠሩ 708 ግለሰቦችም በቁጥጥር ስር ውለው አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው እየተደረገ ነውም ብለዋል።

በተጨማሪም የንግድ ማጭበርበርን በመከላከልና በመቆጣጠር ሂደት ማለትም በኢንተለጀንስ ሥራዎች፣ በድንገተኛ ፍተሻ፣ በቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ቁጥጥር፣ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት፣ በመደበኛ ዕቃ ፍተሻ እና ሰነድ ምርመራ 98.29 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን ጠቁመዋል።

በጠቅላላው በ2017 የበጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በንግድ ማጭበርበር እና በኮንትሮባንድ መንግሥት ሊያጣው የነበረ 107.24 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን ገልጸው፣ ኮንትሮባንድና ንግድ ማጭበርበርን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የኮሚሽኑ ዓቅም እየጎለበተ መሆኑንም ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ አስገንዝበዋል።

በቁጥጥር ስር ከዋሉት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች መካከል አልባሳት፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ የግንባታ እቃዎች፣ ቡና፣ ጥራጥሬ፣ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች እና የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የመዋቢያ ዕቃዎች፣ ጫት፣ አደንዛዥ እጾች፣ መድኃኒት፣ የምግብ ዘይት፣ የውጭ ሀገር ገንዘቦች ይገኙበታል።

የኮንትሮባንድ ዕቃ አዘዋዋሪዎቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስልታቸውን እየቀያየሩ ቢሆንም በጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኞች፣ በፌደራል ፖሊስ፣ በክልል ፖሊስ አባላትና ህብረተሰቡ የጋራ ጥረትና ትብብር በፍተሻ እና በበረራ መያዛቸው ተወስቷል። በኮንትሮባንድ ዝውውር ተሳትፈው የተገኙ 708 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው እየተደረገ ነው።

በቀጣይ ወራትም ኮንትሮባንድ እና ንግድ ማጭበርበር በሀገር ኢኮኖሚ እና በህዝብ ደኅንነት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በጋራ የመከላከል እንዲሁም ጥፋተኛ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አቅጣጫ ተቀምጧል።

ገቢ ለልማት፣ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ደግአረገ
ም/ዋና አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ወርቁ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
እታገኝ አቦሰጥ
ጽሑፍና ሌይአውት ዲዛይን፡- ብራና ማተሚያ ድርጅት
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ
አድራሻ፡- ስልክ 011-6-17-84 90 ኮድ 2133 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et
ኢሜል፡- ethioerca@gmail.com
ፌስቡክ፡- Ministry of revenues of Ethiopia

ለታክስ እና ለጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነፃ ስልክ፡-8199

## የተቃና የትሪሊዮን...

ከገፅ 1 የዞረ



በመሰብሰብ የዕቅዱን 106.7 ማሳካት ተችሏል። በ2017 ግማሽ በጀት ዓመት የተገኘው ከባለፈው ሙሉ በጀት ዓመት ከተገኘው ገቢ የ67 ቢሊዮን ብር ልዩነት አለው። በዚህም ይበል የሚያሰኝ ሥራ መሥራት ተችሏል።

ይህ ውጤት እንዲመዘገብ ገፊ ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ በመንግሥት የተወሰደው የማክሮ ኢኮኖሚ መሻሻያ፣ ማሻሻያው ተግባራዊ እንዲደረግ የተዘረጉ ጠንካራ የአመራር እና የክትትል ሥርዓቶች፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው የተቋማቱ የመፈጸም እና የማስፈጸም ብቃት እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም አቅም እያደገ መምጣት ተጠቃሾች መሆናቸውን ሚኒስትሯ ጠቅሰዋል።

የትሪሊዮን ጉዞውን ዕውን ለማድረግ ከገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ጎን ለጎን የመንግሥት አገልግሎት እና አስተዳደር ማሻሻያ ሪፎርም ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በስምንት ምሰሶዎች የተዋቀረ ፍኖተካርታ ተቀርጾ የፕሮግራም ጽ/ቤት ተደራጅቷል። ይህም ለግብር ከፋዮች ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል።

ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ስኬቶችን ማስቀጠል፣ ተግዳሮቶችን መፍታት እና ከፍ አድርጎ ማቀድ የትሪሊዮን ጉዞውን ለማሳካት አስተዋጽኦቸው የላቀ ነው።

ይህንን ጉዞ ዕውን ለማድረግ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ግብር ከፋይን እና በባህሪውን ለይቶ በአግባቡ ማወቅ፣ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎቶች መስጠት ይቻል ዘንድ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን አሟጦ መጠቀም፣ ታክስን ከማጣጣም ከክልሎች ጋር አንጻር የሚሠሩ ሥራዎች፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት እና የተጀመሩ የቅርንጫፍ ቤቶችን የክትትል እና ድጋፍ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል የሚሉት ተጠቃሾቹ ናቸው።

ባለፉት ስድስት ወራት በሁለቱም ተቋማት የተመዘገቡት ስኬቶች የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲጸድቅ የተገባው ቃልኪዳን ዕውን የሆነበት በመሆኑ ለዚህ ስኬት አስተዋጽዖ ያደረጉ አካላት ሁሉ ሚኒስትሯ ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

17ኛ ዓመት ቁጥር 180 2017 ዓ.ም በነፃ የሚታደል

# እንግዳችን



አዘጋጅ ሽመልስ ሲሳይ

## “የገቢው ዘርፍ ትልቁ የሀገሪቱ የትራንስፎርሜሽን አካል በመሆኑ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት ይኖርብናል”

የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰፊ የቆዳ ሽፋን ካላቸው ክልሎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነው:: በዚህም የተነሳ ከክልሉ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገቢ እንዲሰበሰብ ይጠበቃል:: ይህም ዕውን ይሆን ዘንድ በክልሉ ጠንካራ እና ውጤታማ ሥራ መሥራት ተገቢ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን አስመልክቶ ከክልሉ የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ከአቶ ተስፋዬ ቱሉ ጋር ቆይታ አድርገናል::

**የኦሮሚያ ክልል ሰፊ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ከሌሎቹ ክልሎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ገቢ እንዲሰበሰብ ይጠበቃል:: በዚህ በጀት ዓመትስ ምን ያህል ገቢ ለማግኘት አቅዳችኋል? ይህንንስ ዕውን ለማድረግ ምን ምን ተግባራትን እያከናወናችሁ ትገኛላችሁ?**

እንደተባለው የኦሮሚያ ክልል ሰፊ ነው:: በዚሁም ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ገቢ መሰብሰብ ይኖርብናል:: ለዚሁም ሲባል የተለጠጠ ዕቅድ ይዘናል:: በ2017 በጀት ዓመት 205.5 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅደን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን:: ለዚሁም በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው:: የመጀመሪያው ተግባር በባለፈው በጀት ዓመት የተስተዋሉ ችግሮች እልባት እንዲያገኙ በአንጻሩ የተስተዋሉ ጠንካራ ጎኖች ይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አቅጣጫዎች አስቀምጠናል::

በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረትም ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው:: እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችም አበረታች ውጤቶችን በማስመገብ ላይ ይገኛሉ:: ሁለተኛው ተግባር ጠንካራ የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓትን መዘረጋት ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ጠንካራ የቁጥጥር እና ክትትል ማዕቀፍ ዘርግተን ይህንን ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን:: ሦስተኛው ተግባር ካሁን ቀደም የግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን አስመልክቶ ያለ ችግርን ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን እንገኛለን:: ለዚሁም የረጅም እና የአጭር ጊዜያት እቅዶችን ቀርጸን ወደ ትግበራ ገብተናል:: አራተኛው ተግባር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን ይህም ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል::

**በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች የጸጥታ ችግሮች ይስተዋላሉ:: ይህ በገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር አያጠያይቅም:: ይህንን ችግር ተቋቁሞ ገቢን ለማሳደግ በክልሉ የታየው ቁርጠኝነት ምን ይመስላል?**

ሠላም የሁሉም መሰረት ነው:: እንደተባለው በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የጸጥታ ችግሮች ነበሩ:: በበጀት ዓመቱ የጸጥታ ችግር አለ ብለን እጃችን አጣጥፈን አልተቀመጥንም:: አቅም በፈቀደ መጠን ባለሙያዎቻችን እንዲሁም አመራሮቻችን ጭምር ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር በመሆን በነዚሁ አካባቢዎች ተንቀሳቀሰው ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት አድርገዋል:: በዚሁም አበረታች ውጤቶችን ማስመዘገብ ተችሏል:: ይህንን ችግር ተቋቁመው የተሰጣቸውን ተግባር እና ኃላፊነት በአግባቡ ለተወጡ ባለሙያዎቻችን እንዲሁም አመራሮቻችን በዚሁ አጋጣሚ ላቅ ያለ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ:: በነዚህ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት አንጻራዊ ሠላም አለ:: ይህም ለገቢ አሰባሰብ ሂደታችን አንድ እርምጃ ስለሆነ በዚህ በጀት ዓመት የተሻለ ገቢ እንሰበስባለን የሚል ግምት አለኝ::

**በዚህ በጀት ዓመት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ተግባር ምንድን ነው?**

የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት እየተሠሩ የሚገኙ ተግባራትን ለመግለጽ ሞክሬያለሁ:: እነዚህ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዮች የግብር ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የቅስቀሳ ሥራ በመሥራት ላይ ነን:: ለዚሁም ሲባል ከዋናው መሥሪያ ቤት የቴክኒካል ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎችን መድበን ባለሙያዎቹም ዞን እና ወረዳ ካሉ አካላት በጋራ ሆነው ተልዕኳቸውን እየተወጡ ይገኛሉ::

**ከደረሰኝ ጋር ተያይዞ እየተከሰተ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ማኑዋል ደረሰኝ ላይ መለያ ኮድ (QR CODE) አብሮ እንዲታተም በመንግሥት ተወስኗል:: ይህ ችግሩን ለመቅረፍ ምን ያህል ያግዛል?**

ደረሰኝ ያለመቁረጥ በሴክተሩ ከሚስተዋሉ ጉዳዮች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል:: ይህም ከሚመነጨው ኢኮኖሚ በቂ ግብር እንዳይሰበሰብ ያደርጋል:: ይህም እንደ ሀገር ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል:: መንግሥትም የችግሩን አንገብጋቢነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ችግሩን የሚመጥን መፍትሄ አስቀምጧል:: ይህም በማንዋል ደረሰኝ ላይ ልዩ መለያ (QR CODE) አብሮ እንዲታተም ማድረግ ነው:: የዚህም አሰራር ተግባራዊ መደረግ ችግሩን ለመቅረፍ ጉልህ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ::

ካሁን ቀደም አንዳንድ ሕገ-ወጥ አካላት ሐሰተኛ ደረሰኞችን ተጠቅመው ሕገ-ወጥ ግብይቶችን ሲፈጽሙ ነበር:: በዚሁም መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ያደርገዋል:: ደረሰኝ መጠቀም ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት:: ግብር ከፋይ ግብይቱ በደረሰኝ የሚያከናውን ከሆነ አስተዳደራዊ ወጪውን ይቀንስለታል፣ የንግዱ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር ያስችለዋል፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ታክስ ስለሚወሰንበት ግብር ከፋዩ ባገኘው ልክ ግብር እንዲከፍል ያስችላል:: በተጨማሪም ፍትሃዊና በመተማመን ላይ የተመሰረተ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል:: በሌላ በኩል መንግሥት መሰብሰብ ያለበት ታክስ በአግባቡ እንዲሰብሰብ ያስችለዋል:: ከዚህ ባሻገር በመተማመን ላይ የተመሰረተ



**አቶ ተስፋዬ ቱሉ**
**የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ**

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ ሰሎሞን ወርቁ


# “በስልክ ጠርተን አንሸልምም!”

## ወ/ሮ ማሕሌት አምዴ (የስጋትና ሕግ ተገዥነት ስትራቴጂ ዳይሬክተር)

የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የታክስ ሥርዓትን ለማዘመን፣ የገቢ አሰባሰቡን ለማሳደግ እና በፈቃደኝነት ግብር የመክፈል ባህልን ለማጎልበት ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ ለታማኝ ግብር ከፋዮች ምስጋና እና እውቅናን መስጠት መሆኑ ይታወቃል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ወ/ሮ ማሕሌት አምዴ፤ የስጋትና ሕግ ተገዥነት ስትራቴጂክ ዳይሬክተር ግብር ከፋዮች ከአንዳንድ አጭበርባሪዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

### ሽልማት እና ዕውቅና የሚሰጠው ለማን ነው?

የገቢዎች ሚኒስቴር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለግብር ከፋዮች እውቅና እና ሽልማት እየሰጠ ይገኛል። እነዚህ ግብር ከፋዮች በታክስ ሕግ ተገዥነታቸው እና በበጀት ዓመቱ በሚያበረክቱት የገቢ አስተዋጽዖ የላቀ አፈጻጸም ያላቸው ናቸው። በዚህ መርሐ-ግብር ለመሳተፍ የሚችሉ ግብር ከፋዮች አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች ላይ ታሳቢ ተደርጎ የሚሠራ ነው።

### ሽልማት እና ዕውቅና የሚሰጥበት መስፈርቶች

መሥሪያ ቤቱ እነዚህን ግብር ከፋዮች ለመሸለም በዓለም አቀፍ ደረጃ እያንዳንዱ የታክስ አስተዳደር ከግብር ከፋዮቹ የሚጠብቀው አራት መሠረታዊ የሕግ ተገዢነት ግዴታዎችን መሰረት በማስረግ ነው። እነዚህም፡-

1. በግብር ከፋይነት መመዝገብ እና ለውጦችን ማስመዝገብ፣
2. ግብርን በወቅቱና በትክክል ማሳወቅ፣
3. በወቅቱ ለቀረበ ማስታወቂያ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ወይም ትክክለኛ ደጋፊ ማስረጃዎች ማቅረብ እና አስፈላጊ ለሆነው ጊዜ መያዝ እንዲሁም
4. ግብርን በወቅቱ መክፈል ናቸው።

በእነዚህ አራት መስፈርቶች መነሻነት 12 ሌሎች መስፈርቶችን በመያዝ ምርጫውን እናከናውናለን። እነዚህ መስፈርቶች፡-

- መሰረታዊ የግብር ከፋይ መረጃ /በዋናነት ሙሉ አድራሻው የኢሜል አድራሻን ጨምሮ፣ ግብር ከፋዩ የተሠማራበት ዘርፍ እና የባንክ አካውንት የሚታይ ይሆናል/፣
- ታክስ ማስታወቅ /በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተጠቅሞ በኢ-ታክስ አጠቃቀም ሥርዓት ያለበት ደረጃ/፣
- የግብር ከፋዩ የቅጣት ታሪክ ሁኔታ፣
- የኦዲት ግኝት ልዩነት ሁኔታ፣
- የግብር/ታክስ ስሌት ልዩነት ሁኔታ፣
- የተመላሽ ጥያቄ የልዩነት ሁኔታ፣
- ግብር ከፋዩ ከጡረታና የሥራ ግብር ውጪ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ያበረከተው የገቢ አስተዋጾዖ፣
- ከታክስ ማጭበርበርና ስወራ ጋር በተያያዘ ያለ መረጃ፣
- የግብር ከፋዩ የእዳ አከፋፈል ታሪክ እና ከእዳ ጋር በተያያዘ ያለበት ሁኔታ፣
- ግብር ከፋዩ በጉምሩክ በኩል ያለው የስጋት ደረጃ፣
- ግብር ከፋዩ በጉምሩክ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና የድንገተኛ ፍተሻ መረጃ ታሪክ እና
- በግብር ከፋዩ ላይ በፍትህ ሚኒስቴር ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ የተገኘ መረጃ ናቸው።

### የሽልማት እና የዕውቅና አሰጣጡ ሂደት

መስፈርቶቹ በድንገት ተነስቶ የሚቀየሩ ሳይሆን በየዓመቱ ለሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ተሰጥቶበት በማኔጅመንቱ ይጸድቃል። ግብር ከፋዮችም ሽልማት በሚሰጥበት የግብር ዘመን ላይ ያሳዩት የታክስ ሕግ ተገዥነት ባህሪ ይለካል። ሽልማቱ በሚሰጥበት ዓመት ላይ ከተመዘገበ አዲስ ግብር ከፋይ ውጪ በሕግ ሰውነት ተሰጥቶች በንግድ ሥራ ያለ እና የሒሳብ መግለጫ ያለው ግብር ከፋይ ሁሉ በሽልማቱ ይካፈላል።

እነዚህ የመምረጫ መስፈርቶች እና የግብር ከፋዮች ሙሉ መረጃ ቀድመው በገቢዎች ሚኒስቴር የመረጃ ቋት ውስጥ የሚቀመጡ በመሆናቸው እና ምርጫው የሚካሄደው ከእጅ ንክኪ ነጻ በሆነ በሲስተም ስለሆነ በግለሰቦች ይሁንታ ወይም ክልከላ የሚወሰን አይደለም።

ግብር ከፋዮች የሽልማቱ ተካፋይ በሚሆኑበት ጊዜ ግብር በሚከፍሉበት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፣ በዋናው መ/ቤት ወይም በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል የመርሐ-ግብሩ ተካፋይ መሆናቸውን የሚገልጽ ሕጋዊ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። በሚኒስቴሩ ወይም በኮሚሽኑ በኩል “አስሸልማሀለሁ / እንድትሸለም አደርግሃለሁ/” የሚሉ ሠራተኞች ካሉ ለመሥሪያ ቤቱ ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ ይገባል። ምክንቱም ተሸላሚዎችን በስልክ ወይም በቃል የምንጠራበት አሰራር የለንም። በስልክ ከተጠራም በመርሐ-ግብሩ ላይ እንዲገኙ “መጥሪያዎትን መጥተው ይውሰዱ” የሚል ነው እንጂ በስልክ ጠርተን አንሸልምም መስፈርቶችንም አንጠይቅም።

### ግብር ከፋዮች ተጠንቀቁ

ግብር ከፋዮች በተቋሙ ስም ከሚነግዱ አጭበራባሪዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ እና መረጃዎች እጃቸው ላይ በሚገባበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ወዲያው በማሳወቅ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የጋራ ትብብራቸውን ሊያደርጉ ይገባል። ግብር ከፋዮች አጭበርባሪዎቹን አሳልፎ ለመስጠት በጣም ተባባሪ ከመሆንም ባሻገር ወደ ፖሊስ እና ፍርድ ሲሄድ መረጃ እና ማስረጃቸው በእጃቸው ስለሚገኝ ቀርበው ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

## ባለ ልዩ መለያ ደረሰኝ

ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የንግድ አድራሻ የተለያየ ደረሰኝ እንዲታተም ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነና በእያንዳንዱ ደረሰኝ ላይ ልዩ መለያ QR ኮድ (Unique QR Code) ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ማሻሻያ ቁጥር 188/2017”ን አውጥቷል።

ማንኛውም ታክስ ከፋይ ማሻሻያው ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት አሳትሞ ያልተጠቀመባቸውን ደረሰኞች መጠቀም የሚችለው ማሻሻያ መመሪያው ከወጣበት ከኅዳር 3 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 2 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ባለው ለሦስት ወር ጊዜ ብቻ ነው።አዲሱን QR-code ያለው ደረሰኝ ከወዲሁ ግብር ወደ ሚከፍልበት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመሄድ የኅትመት ትዕዛዝ ጥያቄ በማቅረብ ማሳተም አለበት።በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ደረሰኞችን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ ተመዝጋቢ ለሆነበት የታክስ ባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት በማድረግ ደረሰኞቹ እንዲወገዱ የማመልከትና የማስወገድ ግዴታ አለበት።በአዲሱ የደረሰኝ ህትመት የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ተግባር እና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል: -

### በአዲሱ የደረሰኝ ህትመት የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ተግባር እና ኃላፊነት

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
Berhanena Selam Printing Enterprise

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ደረሰኝ ለማሳተም ወይም የታተመለትን የታክስ ደረሰኝ ለመውሰድ ወደ ማተሚያ ቤት ሲመጣ ታክስ ከፋዩ ደረሰኝ እንዲታተም ከታክስ ባለሥልጣኑ የተሰጠ የደረሰኝ ህትመት መፍቀጃ ቁጥር / ኮድ/ ደብዳቤ የተጻፈለት እና የታክስ ደረሰኝ ለማሳተም የተከፈለበት ደረሰኝ የያዘ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. የህትመት ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ታክስ ከፋዩ ራሱ ወይም ወኪሉ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ደረሰኝ ሲያትም ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ ቢሮዎች ጨምሮ ሊያገለግል የሚችል በታክስ ባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ልዩ መለያየ መለያ ኮድ (Unique QR-code) በእያንዳንዱ የደረሰኝ ቅጠል ላይ በተለያ መለያ ኮድ መታተም የሚገባው ሲሆን ህትመቱ ሲከናወን የልዩ መለያ ኮዱ ወርድ እና ቁመት ቢያንስ 2 ሴንቲ ሜትር ሆኖ በደረሰኙ የቀኝ ራስጌ ላይ መታተም አለበት፤
4. በማንዋል ደረሰኝ (QR-code) አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) የተጋራውን /integrated/ መረጃ ዳታ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማድረግ ደኅንነቱን እና ምስጢራዊነቱን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤
5. የታክስ ደረሰኙ ላይ ስህተት ወይም ልዩነት ሳይኖር ደረሰኞችን ልዩ መለያ ኮድ (Unique QR-code) ያለው ለማተም በማንዋል ደረሰኝ (QR-code) አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) የተጋራውን /integrated ዳታ በትክክል ተቀብሎ የመተግበር ግዴታ አለበት፤
6. በማንዋል ደረሰኝ (QR-code) አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) በኩል ዳታ ሲጋራ ተገቢነት ያላቸውን ሁሉንም የዳታ ጥበቃ ደንቦች እና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፤
7. ልዩ መለያ ኮድ (Unique QR-code) ያለው ታክስ ደረሰኝ ከማተሙ በፊት በማንዋል ደረሰኝ (QR-code) አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) የተጋራውን /integrated/ መረጃ በትክክል መታተሙን ለማረጋገጥ የጥራት ቁጥጥር እርምጃዎችን የመተግበር ኃላፊነት አለበት፤
8. የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የሚያትመው የታክስ ደረሰኝ በራሱ በማተሚያ ድርጅቱ የታተመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ተጨማሪ መለያ ኮድ /feature/ ማተም አለበት፤
9. በሲስተም እንዲታተም ተፈቀደውን እና የታተመውን ደረሰኝ ለገቢ ሰብሳቢ ተቋም ሪፖርት በተዘጋጀው

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# በየዓይነቱ




አዘጋጅ እታገኝ አቦሰጥ

በሰሎሞን ደግአረገ


## እንቆቅልሽ ላይ እንዴት ናችሁ?

እኔን ለመክፈል የመጀመሪያው ሆነ የመጨረሻ ኃላፊነት ያለበት በአንድ ሰው ወይም ገቢውን ያገኘው ሰው ላይ ሲሆን የመክፈል ግዴታ ወደ ሌሎች ሰዎች አይሸጋገርም ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ አያርፍም።እኔ ማን ነኝ?



መልሱን ታውቁታላችሁ? በ0116178490 (2133) ኢጋሩን፡፡

## ሰዎች ስለግብር ምን አሉ?



በሰሎሞን ደግአረገ

## የግብር ቱርፋቶች



በ86 ሚሊየን ብር ወጪ በቀን ከ190 በላይ በባለ 50 ሊትር ሲሊንደር ኦክስጂን ማምረት የሚችል ፋብሪካ በይርጋዓለም ሆስፒታል ህክምና ኮሌጅ ጥር 4/2017 ተመርቆ ሥራ ጀምሯል። ሆስፒታሉ ከሚያመርተው ኦክስጂን ለራሱ ተጠቅም ለሌሎች 10 የአካባቢው ሆስፒታሎች ማቅረብ የሚቻለው መሆኑም የዘገበው ኢ.ዜ.አ ነው።



ከ60 ነጥብ 9 ሚሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ለገሂዳ ወረዳ የተገነባ የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ጥር 3 ቀን 2017 ዓ.ም ተመረቀ መመረቁን ፋና ብሮድካስቲግ ኮርፖሬሽን ዘግቧል።



ለ340 የጸጥታ አካላት የመኖሪያ ቤት መተላለፉን የአዲስ አበበ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ገለጸዋል፡፡



በተጠናቀቀው ግማሽ የበጀት ዓመት ከአራት የነፋስ ኃይል ማመንጫዎች 353 ነጥብ 41 ጊጋ ዋት በሠዓት ማመንጨት መቻሉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡




በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጌዴኦ ዞን ይርጋጨፌ ከተማ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገነቡ የመሰረተ ልማት ተቋማት ተመርቀዋል።



144 የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ምዕራብ ጉጂ ዞን መጠናቀቃቸውን የዞኑ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ገለፀ። የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ገመዴ ጎሎልቻ ለኢ.ዜ.አ እንደተናገሩት በዞኑ በመንግስትና በሕዝብ ተሳትፎ በ2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ወጪ 683 የጤና፣ የትምህርት፣ የውሃ፣ የመንገድ፣ የቢሮና ሌሎች መሰረተ ልማት ግንባታዎች እየተከናወኑ ነው።

## የአሜሪካውያን (የግብር ግዴታዬን አልተወጣሁም) እምነት

በእስክንድር መርሐጽድቅ



አብዛኛዎቹ አሜሪካውያን ኮርፖሬሽኖች እና ሃብታሞች ተገቢውን ግብር እየከፈሉ እንዳልሆነ ያምናሉ።በ2023 የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው፤ ከአስር አሜሪካውያን ስድስቱ ‹‹ለሀገሬ መክፈል የሚገባኝን ያህል ግብር አልከፈልኩም›› የሚል እምነት አላቸው።

ከአሜሪካውያን 56 በመቶዎቹ በሚከፍሉት ግብር ከፌዴራል መንግሥት በምላሹ የሚያገኙትን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ፍትሃዊነቱ የበለጠ እንዲከፍሉ ይገፋፋቸዋል። ይህ በ2021 ከነበረው 49 በመቶ ድርሻ ያደገ ሲሆን ጥቅሙ እንደተለመደው ከቀጠለ ዕድገቱ በየጊዜው እንደሚጨምር አመልካች ነው።

ምንጭ፡-https://www.pewresearch.org/short-reads/2024/04/09/7-facts-about-americans-and-taxes/

## “የገቢው ዘርፍ ትልቁ የሀገሪቱ የትራንስፎርሜሽን...

ከገፅ 3 የዞረ

የታክስ አሰባበሰብ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል:: ለሸማቾችም ደግሞ ለሚገዙት ዕቃ ዋስትና ከመሆን አልፎ የከፈሉት ታክስ በትክክል ወደ መንግሥት ገብቶ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ አንድ ማረጋገጫ መንገድ ነው::

**የገቢዎች ሚኒስቴር እያደረገለቻሁ ያለው ድጋፍ ምን ይመስላል?**

የኦሮሚያ ክልል ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ አጠያያቂ አይደለም:: ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኦፕሬሽን ሥራዎችን ከእኛ ጋር ከመሥራት ጀምሮ ድጋፍ በሚያስፈልጉን ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አብሮን እየሠራ ይገኛል:: በቀጣይም ይሄው ተግባር በበለጠ መልኩ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት::

**የኦሮሚያ ክልል ገቢን ለማሳደግ የገጠር መሬት መጠቀሚያ እና የግብርና ገቢን አስመልክቶ አዋጅ አውጥቶ ነበር:: ይህንን አዋጅ ማውጣቱ ለምን አስፈለገ?**

የገጠር መሬት መጠቀሚያ እና የግብርና ገቢ አዲስ አይደለም:: ይህ ሥርዓት በኢትዮጵያ የታክስ ሥርዓት ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ነው ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው:: አሁን ማሻሻያ አደረግን እንጂ አዲስ አዋጅ አላወጣንም:: በዚሁም አዋጅ ቁጥር 255/2016 ተግባራዊ እንዲደረግ በጨፌ ኦሮሚያ ተወስኗል:: ይህ አዋጅ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነው ካሁን ቀደም አርሶ አደሩ ሲከፍል የነበረው ገቢ አነስተኛ በመሆኑ ነው:: ይሁን እንጂ የአርሶ አደሩ ገቢ በጨመረ ቁጥር የሚሰበሰበው ገቢም ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል:: ለዚህ ሲባል ነው አዋጁ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነው::

**አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ምን ተግባራትን በማከናወን ላይ ናችሁ?**

አዋጁ ተግባራዊ እንዲደረግ ከክልሉ መንግሥት አቅጣጫ ተቀምጧል:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራን እንገኛለን:: ለአብነትም ለአርሶ አደሮቹ ስለ አዋጁ አስፈላጊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር በመሥራት ላይ እንገኛለን:: በቀጣይም ይህንኑ ተግባር አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል::

**ከባለድርሻ አካላት ጋር ያላችሁ ቅንጅት ምን ይመስላል? በተለይ ገቢዎች ሚኒስቴር ጋር ያላችሁ?**

የገቢው ዘርፍ ትልቁ የሀገሪቱ ትራንስፎርሜሽን አካል ነው:: ከዚህ አኳያም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራን እንገኛለን:: ከነዚህም ባለድርሻ አካላት መካከል የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢንቨስትመንት ቢሮ፣ የመሬት አስተዳደር እንዲሁም የፀጥታ አካላት ይገኙበታል:: እስካሁን ከነዚህ አካላት ጋር ባከናወናቸው ተግባራት አመርቂ ውጤት እያስመዘገብን እንገኛለን:: በቀጣይ ጊዜያትም ከነዚህ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ዕቅድ ይዘናል:: ከላይ ከዘረዘርኳቸው ባለድርሻ አካላት በተጨማሪ የዚህ ቁልፍ ሴክተር ባለድርሻ አካላት አብረውን መሥራት ይኖርባቸዋል::

ገቢ ለልማት፡- አቶ ተስፋዬ ቱሉ ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለው::

አቶ ተስፋዬ፡- እኔም አመሰግናለው::

## የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚደግፍ ገቢ...

ከገፅ 1 የዞረ

ብለዋል:: በተለይም የታክስ መሠረት ከማስፋት አንጻር መደበኛ ያልሆነ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችን ወደ ታክስ መሠረት ለማምጣት የብዙ አካላትን ርብርብ የሚፈልግ ነው ያሉ ሲሆን በዚህ ረገድ ያሉትንም ሆነ በፖሊሲ ደረጃ የተጀማመሩ እና መቋጨት ያለባቸው ጉዳዮችን መጨረስ እንዲሁም የታክስ ሕግ-ተገዥነት ሊያሳድግ የሚችል ሥራ በሰፊው መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል::

የገንዘብ ሚኒስትሩ ክቡር አህመድ ሽዴ በመድረኩ እንደገለፁት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በተደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራ ጠንካራ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል። በኢትዮጵያ ከፍተኛ የልማት ሥራዎች መካሄዳቸውንና የተለያዩ ድጎማዎችን ተከትሎ የመንግሥት ወጪ ከፍ ብሏል። ስለዚህ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በአግባቡ መሰብሰብ እንደሚገባም በመድረኩ ገልፀዋል።

## ባለ ልዩ መለያ...

ከገፅ 4 የዞረ

ሲስተም የመላክ ግዴታ አለበት፤

10. ልዩ መለያ ኮድ ያለው ማንዋል ደረሰኝ ሲታተም ከወረቀቱ ላይ በቀላሉ ሊለቅ የማይችል “ኢንክ ጀት (Ink jet)” የሚባል ቀለም የመጠቀም ግዴታ አለበት፤
11. በአካል መጥተው የታተመላቸውን ደረሰኝ የሚወስዱ ግብር ከፋዮች ወይም ወኪሎች ለዚህ ተግባር ብቻ ዝግጁ የሆነ መጋዘን በማዘጋጀት ዴሊቨሪ ሪፖርት (Delivery Report) በሲስተም መላክ አለበት፤
12. የፌደራል፣ የክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ የታክስ ማዕከላቶች የሲስተም ኔትወርክ መቆራረጥ ሲያጋጥማቸው ግብር የከፋዩን የህትመት ጥያቄ በመቀበል ለማተሚያ ድርርጅቱ በኤክሴል (Exel) በማደራጀት ኢሜይል የሚላክበትን ደረሰኝ ከላይ የተገለጹ ኮዶችን በመጠቀም አትሞ ማሳወቅ አለበት፤
13. የሚታተመው የታክስ ደረሰኝ ደረጃውን የጠበቀ እና ጥራቱ የተረጋገጠ መሆን አለለበት፤
14. የታተሙ የደረሰኝ ጥራዞችን ደረጃውን በጠበቀ ማሸጊያ አሽጎ ለስርጭት ማዘጋጀት አለበት፤

**የክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮን ጨምሮ ገቢዎች ሚኒስቴር እና የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የጋራ ተግባር እና ኃላፊነት**

1. በአሰራር ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች እና አዳዲስ አሰራር ማሻሻያዎችን በተናጠል እና በጋራ ይለያሉ፤
2. የጋራ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣ በጋራ ይገመግማሉ፣ የተፈቱትን እና ያልተፈቱትን ችግሮች በመለየት በቀጣይ እንዲከናወኑ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፤
3. ህገ-ወጥ ደረሰኝ ለመከላከል እና የደረሰኝ አጠቃቀምን ለማሻሻል በጋራ ይሰራሉ፤
4. ስለደረሰኝ ህትመት የመረጃ ልውውጥ፣ የህትመት ጥያቄ አቀባበል፣ የስርጭት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
5. የታክስ ደረሰኝ ህትመት ላይ እንደአስፈላጊነቱ ቴክኒካል መስፈርቶች እና መረጃ ይዘት በጋራ በማዘጋጀት እንዲተገበር ያደርጋል።

### የታክስ ምንነት

ታክስ በመንግሥት የሚጣል ህጋዊ ግዴታ ሲሆን ታክስ መክፈል በገዛ ፍላጎትም ብቻ ሳይሆን የአስገዳጅነት ባህርይ ያለው ነው። ታክስ የሚጣለውና የሚሰበሰበው ለጠቅላላ ሕብረተሰብ ጥቅም እንደመሆኑ መጠን መንግሥት በሚያወጣው ወጪ ተጠቃሚ የሚሆነው ታክስ ከፋዩ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሀገሪቱ ዜጎች ናቸው፡፡

የታክስ ሥርዓት ምንነት


የታክስ ሥርዓት የታክስ ህጉን መሠረት በማድረግ በየደረጃው የሚወጡ የአሠራር ሥርዓቶች በታክስ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋይነት ከመመዝገብ ጀምሮ ያሉ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ፣ የኦዲት፤ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓትን ጨምሮ የአገልግሎት አሰጣጥና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት እና ሌሎችን ማጠቃለል የሚገለጽበት የታክስ ሕግ አስተዳደር መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡

የታክስ ሕግ ምንነት

የታክስ ህግ ማለት መንግሥት፤ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚከፍሉትን ታክስ ዓይነት፣ የማስከፈያ መጣኔ፣ የታክስ አወሳሰኑን፣ አሰባሰቡን በአጠቃላይ ታክስ የመክፈል ግዴታንና የግዴታቸውን አፈፃፀም አስመልክቶ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ በጽሑፍ የሚያውጀው የታክስ አስተዳደርና የአሠራር ሥርዓቱ መሠረታዊ መርሆዎች የሚገለጹበት የታክስ ሰነድ ነው፡፡

**የታክስ ዓላማዎች**

- መንግሥት ለጠቅላላ ኅብረተሰቡ ለሚያቀርባቸው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የሚያደርጋውን ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችለውን ገቢ ለማመንጨት፤
- የተረጋጋ ኢኮኖሚ ማስፈን:- መንግሥት ታክስን በመጠቀም የዋጋ ግሽበትና የኢኮኖሚ መቀዛቀዝን ለመቆጣጠር ሊጠቀምበት ይችላል።ይህንንም እውን የሚያደርገው እንደ ሁኔታው የታክስ ማስከፈያ መጣኔዎችን በመጨመር ወይም በመቀነስ ወይም አዲስ ታክስ በመጣል ወይም የተወሰኑ ታክሶችን በማንሳት ሊሆን ይችላል።
- ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍል በማስፈን ማህበራዊ ሚዛንን መጠበቅ:- ገቢያቸው ከፍተኛና ዝቅተኛ በሆኑ ማህበረሰብ መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ልዩነትን ለማጥበብ ብዙ መንግሥታት የኢትዮጵያን መንግሥት ጨምሮ እየጨመረ የሚሄደው የታክስ መጣኔ ሥርዓት ተግባራዊ ያደርጋሉ።በዚህ ዓይነቱ ታክስ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ዜጎች ከፍተኛ የታክስ መጠን እንዲከፍሉ እንዲሁም መካከለኛ ገቢ የሚያገኙት ደግሞ ዝቅ ያለ ታክስ እንዲከፍሉ የሚደረግ ሲሆን ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ዜጎች ደግሞ ከታክስ ነጻ ሊደረጉ ይችላል።ከፍተኛና ዝቅተኛ ገቢ ከሚያገኙት ዜጎች የተሰበሰበውን ታክስ መንግሥት ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ዜጎች ወይም ምንም ገቢ ለሌላቸው ወይም ሥራ አጦችን ለመደጎም ይውላል።
- ሀብት አመዳደብ:- በመንግሥት የሚቀርቡ እንደ መከላከያ፣ ፖሊስ፣ ፍትህ አስተዳደር፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ እና ሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በባህረያቸው ሊከፋፈሉ የማይችሉ ወይም አገልግሎቶቹን ለአንዱ ሰው/ማኅበረሰብ ሰጥቶ ለሌላው መከልከል አይቻልም። ሆኖም የግድ በመንግሥት ሊሠሩ የሚገባው አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል እና ቅድሚያ ሰጥቶ ለሚያከናውናቸው ትኩረት የመስጠት፣ ለግል የሚተውትን የመለየት፣ በጋራ የሚመሩትን የመምረጥ ሥራ አከናውኖ ሀብት የሚመድብበት ሥርዓት ነው፡፡
- ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት:- መንግሥት ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ልዩ ትኩረት የሚገባቸውን የሥራ መስኮችን ለማበረታታት እና በሥራ መስኮቹ ላይ የሚጣለውን ታክስ ሊቀንስ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከታክስ ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል።




By- Shimelis Sisay

By- Solomon Degarege

# Cooperation between Ethiopia and China in the Customs Sector



The General Administration of Customs of China and Shanghai Customs University has provided capacity building training for workers of Ethiopian Customs Commission for one month.

Speaking at the opening and closing of the capacity building training, Ethiopian Customs Commission's Deputy Commissioner, Mr. Azezew Chane, explained that the long-standing and friendly relations between Ethiopia and China continue serve as a foundation for mutual growth and development. This training program stands as an example of our partnership, demonstrating the value of working together to achieve shared goals.

The training program prepared by the Chinese customs administration will enable Ethiopia and China to strengthen their cooperation in the customs sector as well as to acquire knowledge and exchange experience in the field. The bonds we have fostered through this collaboration will endure and inspire even greater achievements in the future according to the deputy commissioner.

The Economic and Commercial Counsellor of Chinese Embassy to Ethiopia, Mr. Xue Wei, said that the Chinese government is working on a program to build the capacity of African customs institutions, and he said that the capacity building training provided to the workers of the Ethiopian Customs Commission is a part of this program. Apart from training, many activities are being carried out to strengthen the cooperation between Ethiopia and China in the customs sector, he added.


## Tax Receipt Usage and Administration Amendment

Whereas, it has become necessary to make a taxpayer use different invoices for each of the businesses categories and each of his business places, and it has become essential to include a unique QR cod on each tax invoice; therefore, the Ministry of Revenues has issued the amendment directive No. 188/2024.

Any taxpayer who printed tax invoices before the coming into force of this Amended Directive and has not used them yet can use them only within three months from November 12/2024 to February 09,2024. The invoice not used within the period given shall be reported to the relevant tax authority and be disposed of.

The new receipt with QR-code should be printed to the branch office where he is already paying tax and submitting a print order request. Each tax invoice must include a unique QR cod when printed; otherwise, it shall not be accepted. The printed enterprise prints a tax invoice, it is a must to take the unique QR code prepared by the tax authority and include it on each invoice sheet. This unique QR cod should be printed on the right header of the invoice with a width and height not less than 2 cm.

## Common Non-Deductible Expenses and Losses



Managing business finances can be a headache, but understanding tax obligations is crucial for ensuring compliance and maximizing deductions. Understanding non-deductible business expenses is crucial to ensuring your company stays on the right side of tax laws. Misclassification can lead to financial surprises, increased audits, and penalties, affecting your bottom line.

### What are some common non-deductible expenses?

Misunderstanding what counts as a non-deductible business expense can lead to costly mistakes. Here are the most common categories of non-deductible expenses you should know according to the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016:

- An increase in share capital of a company or the basic capital of a registered partnership;
- Voluntary pension or provident fund contributions in respect of an employee in excess of 15% of the monthly employment income of the employee;
- Dividends and paid-out profit shares;
- An expenditure or loss to the extent recovered or recoverable under a policy of insurance, or a contract of indemnity, guarantee, or surety;
- A fine or penalty imposed, or punitive damages awarded, for violation of any law, regulation, or contract;
- An amount that a person has transferred, in its financial account, to a reserve or provision for expenditures or losses not yet incurred but expected to be incurred in a future tax year;
- Representation expenditure of an employee in excess of 10% of the employment income of the employee;
- Personal consumption expenditure;
- A loss on the disposal of a business asset by a taxpayer to a related person;
- Expenditure to the extent disallowed under regulations issued by the Council of Ministers and Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016.

## ሕግ-ግብር



አዘጋጅ ሰሎሞን ወርቁ

# ሕግ ወደ ኋላ ይሠራ ይሆን?




ግለሰቦቹ በኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ አክሲዮን ማህበር ያላቸውን የባለቤትነት ድርሻ የተወሰነውን ዕጣ (ሼር) ሸጠዋል። ድርጅቱ በደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይነት የተመዘገበ ነው። ግለሰቦቹም በገቢዎች ሚኒስቴር ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ግብራቸውን እያሳወቁ እየከፈሉ ኖረዋል።

የገቢዎች ሚኒስቴር የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ከመሻሻሉ በፊት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 የተባለ አዋጅ ነበረው።

የገቢዎች ሚኒስቴር ግለሰቦቹ ከሸጡት (ሼር) ላይ በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በደንብ ቁጥር 410/2008 መሰረት በ2010 ዓ.ም የግብር ዘመን ከካፒታል ሽያጭ ካገኙት ትርፍ ላይ አቶ አብነት ገ/መስቀልን 9,422,050.79 ብር፣ አቶ ሙኒር ዱሪን 9,701,141.02 ብር እንዲሁም አቶ ደረጀ የሱወርቅን 6,692,341.43 ብር "ግብር እንዲከፍሉ" በሚል ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል።

ግለሰቦቹ የተባለውን ያህል ገንዘብ መክፈል እንደሌለባቸው በጠበቃቸው አማካኝነት ክርክራቸውን አሰምተዋል። በክርክራቸውም ሁለት መሰረታዊ ቅሬታዎችን አንስተዋል።

የመጀመሪያው በገቢዎች ሚኒስቴር አማካኝነት የተወሰነብን አስገዳጅ የታክስ ውሳኔ ሥነ-ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፤ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55/1/ እና በመመሪያ ቁጥር 127/2009 አንቀጽ 2/5/ መሰረት ቅሬታውን አጣርቶ ለዋና ዳይሬክተር ወይም ለወከለው ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ እንጂ ኮሚቴው ራሱ ውሳኔ የሚሰጥ እንዳልሆነ እየታወቀ በእኛ ላይ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅሬታ ሰሚ ጽ/ቤት ያለሥልጣን ገደቡ አስገዳጅ ውሳኔ ማስተላለፍ ያለአግባብ ስለሆነ "እንዲሻርልን" የሚል ነው።

ሁለተኛው ደግሞ የኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ አክሲን ማህበር የአክሲዮን ድርሻችንን በሽያጭ በምናስተላልፍበት ወቅት በሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 37 (1) (ለ) እና በደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 15 (1-3) መሰረት ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተሰርቶ ባገኘነው ጥቅም ላይ 30% የካፒታል ሽያጭ ትርፍ ተቀናሽ የተደረገልንን የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ (inflation adjustment) የሚፈለግብብንን ክፍያ ከፈጸምን ከሁለት ወር በኋላ እንዲሁም በሰኔ ወር 2009 ዓ.ም ላይ ሙሉ በሙሉ ከከፈልን ከስድስት ወር በኃላ በወቅቱ በሥራ ላይ ባልነበረ ደንብ ቁጥር 410/2008 እና በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በታህሳስ 11/2010 ዓ.ም በተሰጠ ማብራሪያ መሰረት አዋጅ ቁጥር 979/2008ን በሚቃረን መልኩ ወደኋላ ተመልሶ /retroactively/ እንዲፈጸምብን የተወሰነ ውሳኔ ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ አክሲዮኖችን በማስተላለፍ ባገኘነው ጥቅም መነሻነት በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37/1/ እና ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 15/3/ በግልጽ በተደነገገው እና በነበረው አሠራር መመሪያ መሰረት ተቀናሽ የተደረገልን አነስተኛ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ (inflation adjustment) በሕግ አግባብ ተደረገልን በቀድሞ ህጎች የተቀነሰልንን 5% እንድንከፍል መጠየቃችን በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ነሐሴ 18 ቀን 2009 ዓ.ም ታትሞ በወጣው የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 56 ላይ የተደነገገውም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ታህሳስ 11/2010 ዓ.ም ያስተላለፈው መመሪያ ተፈጻሚነታቸው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ላለው ጊዜ እንጂ ወደኋላ ተመልሰው /retroactively/ በእኛ ላይ ተፈጻሚ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።

ታክስ አስከፋዩ መሥሪያ ቤት በበኩሉ በታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 54 መሰረት የቀረበ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማስታወቂያ እንዲመረምር በአንቀጽ 55 እና በመመሪያ ቁጥር 127/2009 መሰረት የተቋቋመው አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታውን ካጣራ በኋላ በሥራ አስኪያጅ ወይም በሚወክልው ኃላፊ አማካኝነት ከጸደቀ በኋላ በአቤቱታ አጣሪው ኮሚቴ ሰብሳቢው ወይም በክፍሉ ኃላፊ መሸኛ ደብዳቤ ተፈርሞ ለግለሰቦቹ እንዲደርስ ተደርጓል። ይህም በመመሪያው ላይ በተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት መሰረት የተፈጸመ ስለሆነ "ቅሬታው የሕግ መሰረት የለውም" በማለት ውሳኔ አስተላልፏል። የግብር ይግባኝ ኮሚሽን ይህንን ጉዳይ "የሚነቀፍ አይደለም" በማለት አጽንቶታል።

ሁለተኛውን ጉዳይ በተመለከተ በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 101 እና የመሸጋገሪያ ድንጋጌው ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት የግብር ዓመት በፊት ላለው የግብር ዓመት በዓዋጅ ቁጥር 979/2008 የተሻሩ ሕጎች ተፈጻሚነት እንዳላቸው ደንግጓል። ይህ ማለት አዋጁ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት የግብር ዘመን በኋላ ላሉት ጉዳዮች ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

በታክስ አስተዳደሩ አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 137 /1/ መሰረት አዋጁ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በተፈጸመ ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት የተሰጠ የታክስ ውሳኔ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለውን ስንመለከት ግለሰቦቹ በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ንዑስ ቁጥር 101 ላይ የተጠቀሰን የተሻሩ ሕጎች ተፈጻሚነታቸን ብቻ መያዛቸው ከታክስ ሕጎች ወደኋላ ተመልሰው የሚፈጸሙበት ባህሪ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው በደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 71 ላይ ተፈጻሚነት ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም ጀምሮ በሚገኝ ገቢ ላይ መሆኑ በግልጽ አስቀምጧል። ይህ በግልጽ በመደንገጉ እና የገንዘብ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያስተላለፈው መመሪያም የሕግ አስተያየት ተጠይቆ በደንቡ ቁጥር 410/2010 አንቀጽ 56/1/ መነሻ የተደረገ እንጂ ብቻውን የቆመ ስላልሆነ ውሳኔው ተገቢ በመሆኑ የግለሰቦቹ ክርክር ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል።

ግለሰቦቹ የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 6 ላይ በተጠቀሰው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ሊደረግልን ሲገባ አልተደገልንም ያሉ ቢሆንም ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተሰጠ ማብራሪያ መሰረት ለደረጃ (ለ) ግብር ከፋዮች ዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የማይያዝ መሆኑን በግልጽ በማስቀመጡ ግለሰቦቹ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ስለሆኑ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ሳይደረግ በገቢ ግብር ደንብ 410 መሰረት መወሰኑ አግባብ ነው።

ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 71 ተፈጻሚነት የሚኖረው ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ካለው ግብር ዘመን መሆኑን በግልጽ ባስቀመጠው መሰረት ግለሰቦቹ እንዲከፍሉ የተጠየቁት የግብር ዘመን 2009 ዓ.ም ግብርን በመሆኑ ይህንን የግብር ዘመን የወጣው ገቢ ግብር ደንብ ያካተተውና የምድብ (ለ) ግብር ከፋዮች የዋጋ ግሽበት እንደማይያዝላቸው ይልቁንም ለምድብ "ሀ" ግብር ከፋዮች እና የአክሲዮኖች የማስተላለፊያ ዋጋ ላይ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንዲደረግ የሚፈቅደው በማንቀሳቀሱ ንብረቶች ላይ ነው። በግለሰቦቹ በኩል የቀረበው አክሲዮን ዋጋ ግሽበት በሕጉ ያልተሸፈነ በመሆኑ ግብር እንዲከፍሉበት መጠየቁ በሕጉ አግባብነት ያለው ስለሆነ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ እንዲያሰናብተን በማለት ተከራክሯል።

የታክስ ሕጎች ባህሪያቸው ሲታይ ለተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም ለተከናወኑ ሥራዎች የሚፈለግባቸውን ግብር ወደ ኋላ ሄደው የሚጠየቁ በመሆናቸው ከአዲሶቹ የታክስ ሕጎች እና ደንቦች መረዳት እንደሚቻለው ከወጡበት ጊዜ ወደ ኋላ እየሄዱ አፈጻጸማቸው እንደሚጀምር በግልጽ የሚያስቀምጥ ከመሆኑ ባሻገር በግለሰቦቹ እንደተጠቀሰው እንደ ወንጀል ሕግ ድንጋጌ ዓዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል መባሉ የታክስ ሕጉን ባህሪ እንዲሁም ግብር የሚጠየቅበትን ጊዜ አንድ ግብር ከፋይ በአንድ ግብር ዘመን ሥራ ሠርቶ ገቢ ካገኘ በኋላ ወይም ገቢ ያገኙባቸውን ዘዴዎች በማስላት ባለፉት ጊዜያት ላገኘው ገቢ ግብር ይፈለግብሀል በማለት የሚጠየቅ የሕግ ሥርዓት በመሆኑ ለግለሰቦቹ የተሰጣቸው ውሳኔ በአግባቡ ነው እንዲባልልን ብሏል።

ግለሰቦቹ ጉዳዩን ይግባኝ በማለት እስከ ሰበር ፍርድ ቤት ያደረሱት ሲሆን የሰበር ፍርድ ቤትም የታችኞቹን ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕግ ስህተት እንዳለበት እና እንደሌለበት በመመርመር ስህተት እንደሌለባቸው በማረጋገጥ ግለሰቦቹ የተባለሉትን ያህል የዕጣ (ሼር) ሽያጭ ትርፍ ግብር እንዲከፍሉ ውሳኔውን አጽንቷል።

ምንጭ: - በገቢዎች ሚኒስቴር የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት